

ጥያቄዎች በተማሪዎች ለተማሪዎች

MY SCHOOL DC
የሕዝብ ት/ቤት ሎተሪ
MySchoolDC.org

መግቢያ

በዲስትሪክቱ ውስጥ ካሉት ብዙ የሕዝብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማራጮች በመኖራቸው፣ ተማሪዎች የእኔ ትምህርት ቤት ነው ብለው መጥራት የሚፈልጉትን ትምህርት ቤት ለማግኘት የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለባቸው። ከፍተኛ ውጤት ያላቸው በ8ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ቡድን እርስዎ መጀመር እንዲችሉ እንዲረዳዎት ይህንን የጥያቄዎች ዝርዝር አዘጋጅተዋል። መሰረታዊ መረጃ ለማግኘት በ **MySchoolDC.org** የትምህርት ቤት የአንላይን ፕሮፋይልን ይጎብኙ፣ እና የትምህርት ቤት ሰራተኞን መጠየቅ የሚፈልጉ ጥያቄዎች አጠገብ የምርጫ ምልክት ያስቀምጡ።

እነዚህን ጥያቄዎች ወደ EdFEST፣ የትምህርት ቤት ዝግጅቶች እና የትምህርት ቤት መክፈቻ ቤቶች ጭምር ይዘዋቸው እንደሚሄዱ ያረጋግጡ!

የትምህርት ቤት ፖሊሲዎችን እና አሰራሮችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

- ☐ የትምህርት ቤቱ ፖሊሲዎች ምን ያህል ጥብቅ ናቸው?
- ☐ ለምሳ ምን ታቀርባላችሁ?
- ☐ እያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ ምን ያህል ጊዜ ነው?
- ☐ የባህሪ አስተዳደር ፖሊሲ ምንድን ነው?
- ☐ ትምህርት የሚጀምረው ስንት ሰዓት ነው?
- ☐ ትምህርት ቤት ስሄድ ስልኬን እንድይዝ ይፈቀድልኛል?

ጥያቄዎች ለተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

- ☐ ለትምህርት ቤታችሁ ለማመልከት የሚያስፈልጉት መስፈርቶች ምንድን ናቸው?
- ☐ ወደ ትምህርት ቤታችሁ ለመግባት ዝቅተኛው GPA ምንድነው?
- ☐ የግለሰብ ቃለ መጠይቅ ወይም የቤተሰብ ቃለ ምልልስ ምን ይመስላል?

የተማሪ ተሳትፎን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

- ☐ የተማሪ-መምህር ጥምርታ ምንድነው?
- ☐ ትምህርት ቤታችሁ የሚያዝናና ነው?
- ☐ የመስክ ጉዞዎችን እና አዝናኝ እንቅስቃሴዎችን ያቅዳሉ ወይም ያስተናግዳሉ?
- ☐ በውጭ አገር ጥናት ፕሮግራም አለ?
- ☐ የስፖርት ቡድኖቹን ለመቀላቀል አስቸጋሪ ናቸው?
- ☐ በትምህርት ቤታችሁ የከፍተኛ ተሳትፎ ፕሮግራም አላችሁ?

የትምህርት ቤት ባህልን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

- ☐ ምን ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች አላችሁ?
- ☐ ምን ዓይነት ስፖርቶች አላችሁ?
- ☐ በትምህርት ቤታችሁ ዩኒፎርም ያስፈልጋል?
- ☐ የእቃ ማስቀመጫ ሎከሮች አሉ?

የትምህርት ቤት ትምህርት ሥርዓት የሚመለከቱ ጥያቄዎች

- ☐ መምህራን ብዙውን ጊዜ ምን ያህል የቤት ሥራ ይሰጣሉ?
- ☐ ሥራው ምን ያህል ከባድ ነው?
- ☐ የተማሪ መርሃ ግብር ምሳሌ አላችሁ?